# ጉባኤ ኬልቄዶን

እንደ እኅቶቿ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት (የግብፅ የሶርያ የአርመንና የህንድ) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔና ቀኖና አልተቀበለችውም አትቀበለውምም። ነገር ግን ከጉባኤው አስቀድሞ በጉባኤው ጊዜ ከጉባኤውም በኋላ የነበረውን ኹሉ ኹኔታ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አንባቢዎች እንዲያውቁት ከማለት እዚህ ላይ ምዕራፍ ሰጥተዋል። በዚህ ምዕራፍ የማናያቸው ነጥቦች፤

1. የዲዮስቆሮስ የሕይወት ታሪክ ባጭሩ፣
2. የአውጣኪና የፍላብያኖስ ጠብ፣
3. የአውጣኪ ወመገዝ (በጉባኤ አድያም)፣
4. የ449 ዓ.ም የኤፌሶን ሲኖዶስ፣
5. የልዮን ጦማር ወደ ፋላብያኖስ፣
6. የጉባኤ ኬልቄዶን መሰብሰብና የቅዱስ ዲዮስቆሮስ አላግባብ መወገዝ፣
7. የመለካውያን ምሥጢረ ሥጋዌ፤ የባሕርይ ትርጒም በተዋሕዶዎችና በመለካውያን፣
8. ከዲዮስቆሮስ በኋላ ያዕቆብ ዘእልበረዲና ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ ያሳዩት ተጋድሎ ነው።

ቅዱስ ቄርሎስ የእስክንድርያን መንበረ ማርቆስ ለ32 ዓመታት ያህል አገልግሎ በ444 ዓ.ም ዐረፈ። በመንበሩም ሊቀ ዲያቆኑ የነበረው ወዳጁና ደቀመዛሙሩ ዲዮስቆሮስ ተመርጦ ተሾመ። ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ለመንበረ ማርቆስ 25ኛ ፓትሪያርክ መኾኑ ነው። ዲዮስቆሮስ በትውልዱ ግብጻዊ ነው። በሙያውም ኾነ በትሩፋቱ ይህ ቀረህ የማይባል ስለ ነበር፤ በመላዋ ግብጽ በመካከለኛው ምሥራቅና በታናሽ እስያም ከፍ ያለ ዝና ነበረው። በሃይማኖትም የቅዱስ አትናቴዎስንና የቅዱስ ቄርሎስን ፈለግ ይከተል ስለነበር ለተዋሕዶ ሃይማኖት ቀናተኛና ተቆርቋሪ መናኝ መነኩሴ ነበር። ባለፈው ምዕራፍ እንደገለጥነው ገና ሊቀ ዲያቆን ሳለ መምህሩን ቄርሎስን ተከትሎ ንስጥሮስ የተረታበትን የኤፌሶን ጉባኤ ተካፍሏል። ዲዮስቆሮስ ከአራቱ ታላላቅ የእስክንድርያ ፓትርያርኮች አንዱ ነው። «አትናቴዎስ ቴፍሎስ ቄርሎስና ዲዮስቆሮስ» ላቲኖችና ግሪኮች እነዚህን አራት አባቶች ኃይለኞች ናቸው እንደ ማለት አራቱ ፈርኦኖች ይሏቸዋል። የቅናት የምቀኝነት አነጋገር በቅዱሳን ላይ የተጣለ አጉል ዘርቅ ነው።

ዲዮስቆሮስ በመንበረ ማርቆስ እንደ ተቀመጠ የታናሽ እስያ ግሪኮች ይልቁንም ቄርሎስን ሲቃወሙ የኖሩ እነ ቴዎዶሪጦስ በውዳሴ ከንቱ ለማግባባት ቄርሎስን እያኮሰሱ እሱን እያሞገሱ የሹመት ያዳብር መልእክቶች ላኩለት። ዲዮስቆሮስ ግን ከእምነቱ ወደኋላ የማይል በውዳሴ ከንቱ የማይጠለፍ መንፈሳዊና ታማኝ አባት ስለነበር ሐሳባቸውን አልተቀበለውም እነሱም በዲዮስቆሮስ ዘንድ ተሰሚነት ስላላገኙ የዲዮስቆሮስንና የመንበረ ማርቆስን ስም የሚያጎድፉበት ምክንያት መፈለግ ጀመሩ። በኤፌሶን ጉባኤ 431 ዓ.ም የንስጥሮስ የኹለት ባሕርይ ትምህርት ከተወገዘና የተዋሕዶ ሃይማኖት ከተደላደለች በኋላ ምንም እንኳ ውስጥ ውስጡን ሽኩታ ባይቀርም ለ17 ዓመታት ያህል በቤተ ክርስቲያን አዲስ ክሕደት አልተሰማም ነበር፤ ከዚህ በኋላ (ከ447-449) በቍስጥንጥንያ ያንድ ገዳም አበ ምኔት የነበረ ግሪካዊ መነኩሴ ነው። ንስጥሮስ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ በነበረበት ጊዜ ትምህርቱን ሲቃወምና ሲከራከር የኖረ ነው። ኋላም ከንስጥሮስ የኹለት ባሕርይ ትምህርት የራቅሁ መስሎ ኹለት ባሕርያት ማለት የሥጋና የመለኮት ባሕርያት ተቀላቅለው ተጣፍተዋል፤ የአሪስቶትልን የቅመማ ሕግ በምሥጢረ ሥጋዌ አስገብቶ ማስተማር ጀመረ። አውጣኪ ዘወትር በትምህርት ሥጋና መለኮት በተዋሐዱ ጊዜ መለኮት ሥጋን ውጦታል መጦታል እያለ ባደባባይ ይሰብክ ነበር። በአውጣኪ ዘመን የነበሩ የቤተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣኖች በእስክንድርያ ፓትርያርክ ዲዮስቆሮስ በሮም ፓፓ ልዮን በቍስጥንጥን ፍላብያኖስ ሊቀ ጳጳስ ነበሩ።

ፍላብያኖስ አውጣኪንና ትምህርቱን በቅርብ ቢያውቅም እንደተለመደ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን ሳይጠራ የሀገረ ስብከቱን ኤጲስ ቆጶሳት ብቻ በጉባኤ አድያም ሰብስቦ አወገዘው። አንዳንድ የታሪክ ሰዎች እንደሚሉት ፍላብያኖስ አውጣኪን በችኮላና በድብቅ ያወገዘው አውጣኪ ንስጥሮስን ከመጥላቱ የተነሣ የቍስጥንጥንያን መንበር ይቃወም የነበረ ደፋር መነኩሴ ስለነበር በግል ቂም ወይም የንስጥሮስን በቀል ለመወጣት ሳይኾን አይቀርም ይላሉ። ነገር ግን ምንም እንኳ አውጣኪ ዐይነ ደረቅ መናፍቅ በመኾን እንደ አርዮስ እንደ መቅዶንዮስና እንደንስጥሮስ በመላው የአብያተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣኖች ፊት ቀርቦ መጠየቅና መወገዝ ነበረበት። ይህም ካለመኾኑ የተነሣ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉዳዩን ስላላወቁት አውጣኪ የቄርሎስን ሃይማኖት ስለ መሰከርኩ በከንቱ ተወገዝኩ ብሎ ለቤተ መንግሥት ይግባኝ አለ።

ከይግባኙ በኋላ ጠቡ አሁንም የተነሣው በዚያው በቍስጥንጥንያ ስለኾነ እንደ ተለመደው በእስክንድርያ ፓትርያርክ በዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ እንዲታይለት ሲል ንጉሡ ለእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንና ለሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት መልእክት ላከ። በዚህ ጊዜ ዲዮስቆሮስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ እንደመኾኑ መጠን ጉባኤ ሰብሳቢ ነበር። የጉባኤውም ሰብሳቢ እንደመኾኑ መጠን ቀደም አድርጎ ወደ ኤፌሶን መጣ። አብረዉት ከእስክንድርያ የመጡት 23 ኤጲስቆጶሳት ሲኾኑ ከነዚህ አምስቱ በጉባኤ ኤፌሶን (431) የነበሩ ናቸው። ከነዚህም ሌላ ከሶርያ በአባ በርሶማ የሚመሩ አያሌ ኤጲስ ቆጶሳትና ከሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት የመጡ ነበሩ። ኹሉም ሰዓቱን አክብሮ በጉባኤው ላይ ሲገኝ የሮማው ፓፓ እንደራሴዎች ግን ዘግይተው ደረሱ፤ ለምን እንደዘገዩ እርግጠኛው ባይታወቅም የክርስቶስ እንደራሴ ነኝ የሚለው የሮማው ፓፓ እያለ ግብጻዊው ዲዮስቆሮስ የጉባኤው ሰብሳቢ በመኾኑ ተኮርፎ ሳይሆን አይቀርም። ነገር ግን እስከዚያ ድረስም ቢኾን በተደረጉት ሦስት ሲኖዶሶች ሊቃነ መናብርት የነበሩት የእስክንድርያ ፓትሪያርኮች ስለ ነበሩ ፓፓውን የሚያስቀጣውና የሚያስኮርፈው ጉዳይ አልነበረም። የቍስጥንጥንያው ፍላብያኖስም አልመጣም፤ ያልመጣበት ምክንያት እሱ ያወገዘው ያውጣኪ ጉዳይ እንደገና እንዲታይ በመወሰኑ እልክ ይዞት ሳይኾን አይቀርም።

ያም ኾነ ይህ ዲዮስቆሮስ በጊዜው የመጡትን 135 ኤጲስቆጶሳት ይዞ ነሐሴ 8 ቀን 449 ዓ.ም በኤፌሶን ጉባኤ አደረገ። ይህች ኤፌሶን ከ18 ዓመት በፊት በቄርሎስ መሪነት 200 ሊቃውንት ተሰብስበው የንስጥሮስን የኅድረት ትምህርት ያወገዙባት የተዋሕዶን እምነት ያጸኑባት ቦታ ናት። ጉባኤው የተደረገው ያን ጊዜም አኹንም በእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። አውጣኪ ወደ ጉባኤው ቀርቦ ስለሚያምነው እምነት ሲጠየቅ የተወገዝኹት በሃይማኖቴ ጉድለት ተገኝቶብኝ ሳይኾን ንስጥሮስን እቃወም ስለነበር

በግል ቂም ነው እንጂ እምነቱም ትምህርቱም የሠለስቱ ምእትና የቅዱስ ቄርሎስ ነው ሲል ቃሉን በመሐላ ሰጠ:: አንድ ሰው እምነቱ ይኽ ነው ሲል አይደለም፤ ዋሽተሀ ነው ማለት ስለማይቻል ጉባኤው ለጊዜው አውጣኪን ከግዝቱ ፈትቶ በቤተ ክርስቲያን የነበረውን ሥልጣን መለሰለት::

ከዚህ በኋላ ዲዮስቆሮስ የሚከተለውን ቃል ለጉባኤው አሰማ:: «ከኒቅያ እስከ ኤፌሶን በጉባኤ ተሰብስበው አባቶቻችን ከወሰኑት ሃይማኖት ሌላ የሚጨምር የሚቀንስ ወይም የሚያሻሽል ቢኖር የተወገዘ ይኹን:: የሦስተኛው ጉባኤ ቀኖና በኒቅያ ጉባኤ ከተወሰነው አንቀጸ ሃይማኖት ሌላ የሚጨምር ወይም የሚቀንስ የተወገዘ ይኹን ከሚለው ጋር አንድ ነው፤ ስባተኛውን የኤፌሶን ቀኖና ተመልከት:: በዚህ ጊዜ የነበሩት አባቶች ኹሉ «ዲዮስቆሮስ የተዋሕዶ ሃይማኖትና የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ጠባቂ ዲዮስቆሮስ ታላቁ ዲዮስቆሮስ ገናናው!» እያሉ አመሰገኑት::

ይህን ውሳኔ ሲሰማ ልዮን ጉባኤውን ጉባኤ ፈያት ብሎ ሰየመው:: ይህንም ያለበት ምክንያት የሱ መልእክተኞች ስላለተሳተፉበት ነው:: የጉባኤው መሪ ሊቀ መንበር የነበረውን ዲዮስቆሮስንም አወገዘው:: ልዮን በዚህ ብቻ አልተወሰነም በቊስጥንጥንያው ፍላብያኖስም የመንፈቀ ንስጥሮሳውያንን የኹለት አካል ኹለት ባሕርይ ትምህርት መልኩን ለውጦ በቅፋፍ ጽፎ ላከለት:: መልእክቱም እንዲህ የሚል ነበር «የክርስቶስ ኹለት ባሕርይ ኹለት ህላዌ አንድ አካል አለው ብለን እናምናለን:: **duae naturae et substantiae in unan personam** አካልና ባሕርይ የተለያዩ ናቸው::

ከአካል የተለየ ባሕርይ ከባሕርይ የተለየ አካል የለም ካልን ግን ባሕርይን ኹለት እንዳልን አካልን ኹለት ማለት ይኖርብናል፤ ይኸውም እንደ ንስጥሮስ ማለት ነው:: ወይም አካልን አንድ እንዳልን ባሕርይንም አንድ ማለት ይኖርብናል፤ ይኸውም እንደ ቄርሎስ ማለት ነው:: ኹለቱ ባሕርያት በመተባበር የየራሳቸውን ድርሻ ይሠራሉ:: «መለኮት ይገብር ግብረ መለኮት ትስብእት ይገብር ግብረ ትስብእት» መለኮት የመለኮትን ሥጋም የሥጋን ሥራ ይሠራል::» የሚል ጦማር ነበር::

በጦማሩ እንዳየነው መከራ የተቀበለው ሥጋ፤ ተአምራት ያደረገው መለኮት እንደኾነ ታትቶ ቀርቧል:: ፍላብያኖስ ግን የቊስጥንጥንያ መንበር ከፍ ለማድረግ በነበረው የግሪኮች ጥረት ልዮንን ተባበረን ለማለት ከሱም ሳለመቃቃር እሱ የሚለውንም ላለመቃወም ብሎ ተጠንቅቆ መልስ ሲሰጥ የቄርሎስን ትምህርት በማይቃወም ኹኔታ ተናግሯል:: «የፍላብያኖስ መልስ ከሥጋዌ በኋላ ባንድ አካል፤ ባንድ ከዊን ከኹለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የኾነውን አንድ ክርስቶስን እናምናለን ብሏል»

ከዚህ በኋላ ፍላብያኖስ ሙቶ በመንበሩ አናቶሊዮስ ተተካ:: ዲዮስቆሮስም ልዮን ለፍላብያኖስ የላከውን መልእክት (ጦማር) በሰማ ጊዜ ንስጥሮሳዊ ነህ ብሎ አወገዘው:: ከዚህ በኋላ ላቲኖችና ግሪኮች አንድ ላይ ኾነው በእስክንድርያ የቅዱስ ማርቆስ መንበር ላይ ማሴር ጀመሩ:: ይኽ ሁሉ ግር ግር በፊት የነበረውን የመንበር አቀማመጥ ተራ አፋልሶ ማለት «ሮም እስክንድርያ አንጾኪያ» የነበረውን «ሮም ቊስጥንጥንያ እስክንድርያ» ለማለት ቊስጥንጥንያን ሥርዋጽ ለማስገባት ነው::

አውጣኪ ለጊዜው በተንኮል ሃይማኖቴ ኦርቶዶክስ ነው ቢልም ትንሽ ቆየት ብሎ የውላጤ ትምህርቱን ለማስፋፋት የውስጥ ለውስጥ ዘመቻ ያካሒድ ጀመረ፤ የቃል ለሥጋ የሥጋም ገንዘብ ለቃል የሆነው በተዋሕዶ መኾኑን ሳይገነዘብ አውጣኪ መላልሶ አክሮና አመንችኮ የሚናገረው «የቃል ገንዘብ ለሥጋ የኾነው በውላጤ ነው እያለ ነበር:: ይህም ማለት መለኮት ሥጋን ዋጠው መጠጠው ማለት ነው:: ይህ የአውጣኪ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያኖች ዘንድ ቊጥሩ ከመናፍቃን እንጂ ከቤተ ክርስቲያን አባቶች አይደለም::

ልዮንና ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ተወጋግዘው እንዳሉ ግሪኮችም በሁለቱ መጣላት ቊስጥንጥንያን ከተራ ቊጥር ለማስገባት አሰፍስፈው ሳሉ በ450 ዓ.ም ንጉሡ ቴዎዶስዮስ ከፈረስ ላይ ወድቆ ሞተ:: እሱ ሲሞት እኅቱ ብርክልያ (ፑልኬሪያ) የአባቷን ጀኔራል መርቅያንን አግብታ ነገሠች:: ይህች ሴት ብልጣ ብልጥ ስለ ነበረች ወንድሟ በሕይወት ሳለም የመንግሥቱን አስተዳደር የምትመራው እሷው እንደ ነበረች ይነገርላታል:: ቴዎዶስዮስ በተፈጥሮው ፈዛዛ ነበርና፤ ኋላ ግን አውዶክያስን ሲያገባ ሚስትና እኅት ባመስማማት እኅቲቱ ከቤተ መንግሥት ወጥታ እንደ ግዞተኛ ሁና ትኖር ነበር:: ወንድሟ በሞተ ጊዜ ልጅ ስላልነበረው አልጋው ወደሷ ተዛወረ ብርክልያም ሆነች ባሏ መርቅያን ከነገሡ ጀምሮ በቴዎዶስዮስ ጊዜ የነበረውን ለማፍረስና የራሳቸውን ስም የሚያስጠራ አንድ ሥራ ለመሥራት ቸኩለው ነበር:: ይህም በመሪዎች ዘንድ ሁልጊዜ የሚታይ የውዳሴ ከንቱ ጠባይ ነው:: ያን ጊዜ የነበረው የነገሥታት ጀብዱ በቤተ ክርስቲያን ጣልቃ እያገቡ የቤተ ክርስቲያንን ዶግማ ማፋለስና ለሐሳባቸው የሚስማማቸውን መሾም አልስማማም ያለውን ግን ማዋረድ ማጋዝና መግደል ነበር:: ይህንን ፍላጎታቸውን ለማሟላት ባልና ሚስት አልጋውን እንደያዙ ከሮማው ፓፓ ልዮን ቀዳማዊ ጋ የደብዳቤና የመልእክተኞች ልውውጥ ማድረግ ጀመሩ:: ልዮንም ንስጥሮሳዊ ትምህርቱን ለማደላደል አመች ጊዜ ሆነለት:: ወዲያውም በ451 ዓ.ም በኬልቄዶን (ታናሽ እስያ) ጉባኤ እንዲደረግ የቊስጥንጥንያ ቤተ መንግሥትና እነልዮን ስምምነት አደረጉ:: ከጉባኤው ጥቂት ቀደም ብሎ ልዮንና መርቅያን የቊስጥንጥንያውን አናቶሊዮን ጨምረው ተወያይተው ነበር::

የኬልቄዶን ጉባኤ ዓላማው ምን እንደሆነ እንዳለፉት ጉባኤዎች ግልጥ ምክንያት አልነበረውም:: ከውጤቱ እንደምንረዳው ግን ሁለት ነገሮች አሉበት:: ከነዚህ አንዱ ከላይ እንዳልነው የእስክንድርያን መንበር ዝቅ አድርጎ ተራ ያልነበረውን ቊስጥንጥንያን ባለ መንበር ለማድረግ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ በ431 ዓ.ም በኤፌሶን ጉባኤ የተወገዘውን የንስጥሮስ ትምህርት በአዲስ ስም ሰይሞ ለማደስ ነው::

ያም ሆነ ይህ የኬልቄዶን ጉባኤ ጥቅምት ስምንት ቀን 431 ዓ.ም እንዲሆን ተወሰነ:: በተባለው ቀን 636 ሰዎች ተሰበሰቡ:: (ይህ ቊጥር የ318ቱን ሊቃውንት ቊጥር ያጥፋል ይህም የኾነው ጉባኤው ከኒቅያ ይበልጣል ለማለት ነው::) ጉባኤውን ያዘጋጁትም የቤተ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች የጦር አለቆች ናቸው:: የጉባኤው ሊቃነ መናብርት የነበሩት የልዮን እንደራሴዎች የቊስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ አናቶሊዮስና ሌሎች የመንግሥት ሹማምንትና የጦር አለቆችም ነበሩበት:: በዚህ ጉባኤ ለመገኘት ዲዮስቆሮስም ከእስክንደርያ መጣ፤ 25 ኤጲስ ቆጶሳት ተከትለዉት ነበር:: ከነዚህም ብዙዎቹ ከ20 ዓመታት በፊት ከቄርሎስና ከሱም ከራሱ ጋር አብረው በኤፌሶን ጉባኤ የተሳተፉና የተዋሕዶን ምሥጢር አጣርተው የሚያውቁ ነበሩ::

ይህን ጉባኤ በንስጥሮሳዊነት ሲያሳሙት የሚኖሩ ምክንያቶች አሉ:: እነሱም ሀ/ 431 ዓ.ም በኤፌሶን በንስጥሮስነታቸው የተወገዙ ሰዎች ወደዚህ ጉባኤ እንዲመለሱ መደረጉ ለ/ የልዮን ጦማር ያዘለው መልእክት ግልጥ ያለ ንስጥሮሳዊ ስለኾነ ነው::

ጉባኤው ከመጀመሩ በፊት የጉባኤው ተሳታፊዎች ሁሉ ቦታ ቦታቸውን ይዘው እንደ ተቀመጡ በሊቀ መንበርነት የተሠየሙት የሮም መልእክተኞች የሚከተለውን ተናገሩ «የክርስቶስ እንደራሴ የጴጥሮስ ወራሽ የመላዋ ቤተ ክርስቲያን ራስ ቅዱስ ቅዱሳን አባታችን ልዮን ቀዳማዊ ያዘዙን ትእዛዝ አለ፤ ይኸውም ከአመጸኛውና ከከሐዲው አባታችንን በድፍረት ካወገዘው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ከዲዮስቆሮስ ጋር አብረን በጉባኤ እንዳንቀመጥ ነው:: ዲዮስቆሮስ በዚህ ጉባኤ ከተቀመጠ እኛ ወጥተን እንኼዳለን አሉ:: ይህን ተናግረው ሲጨርሱ በግልምጫና በደም ፍላት የልዮን ደጋፊዎች ሁሉ ተነሥ! እዚህ መቀመጥ የለብህም፤ ተከሳሾች የሚቆሙበት ቦታ ቁም! ብለው በዲዮስቆሮስ ጮሁበት ዲዮስቆሮስም በዚህ ጊዜ ከተቀመጠበት ተነሥቶ የሚከተለውን ተናገረ:: አንድ ባሕርይ ማለታችን ሁለቱን አጣፍተን አይደለም (እንደ አውጣኪ) ወይም አንዱን ከሌላው ለይተን ገንጥለን አይደለም (እንደ አቡሊናርዮስ) ለውጠንም አይደለም ጉሰት ሚጠት ቱሳሔ የሚል ቢኖር የተወገዘ ነው አለ:: ይህን በተናገረ ጊዜ ላቲኖችና ግሪኮች አውጣኪም ያለው ይህንኑ ነበር ዲዮስቆሮስም ይህንኑ አለ! ውጣ! ውጣ! እያሉ ጮሁበት:: በዚህ ጊዜ እሱም የምንነቀፈው በንስጥሮስ ዘንድ ብቻ ነው ብሎ መንበሩን ላለማስደፈር ውጣላቸው፤ ሁለተኛም ወደነሱ አልተመለሰም::

ዲዮስቆሮስ ከወጣ በኋላ ከ20 ዓመታት በፊት በ3ኛው ጉባኤ ከንስጥሮስ ጋር የተወገዙት እነ ቴዎዶሪጦስና እነ ኢባን በጉባኤው ሙሉ የአባልነት መቀመጫ እንዲሰጣቸው ተፈቀደላቸው፤ ይልቁንም ቴዎዶሪጦስ በዲዮስቆሮስ ላይ የማቀርበው ልዩ ክስ አለኝ ብሎ ተናግሮ ስለ ነበር ግሪኮችም ሆኑ ላቲኖች እንደ ጠላት የቆጠሩት ዲዮስቆሮስን የሚያጋልጥልን መስሏቸው «አክሲዮስ አክሲዮስ» ይደልዎ! ይደልዎ! እያሉ ተቀበሉት:: ጉባኤውን ንስጥሮሳዊ ካሰኙት ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው (ንስጥሮሳውያን የጉባኤው አባል በመኾናቸው)::

በዚህ ጊዜ ማለት ንስጥሮሳውያን እነ ኢባን የጉባኤው አባላት እንዲሆኑ በተፈቀደ ጊዜ ከቄርሎስ ጋር በኤፌሶን ጉባኤ የነበሩት አረጋውያን ጳጳሳት በሙሉ ድምፅ በአንድ ላይ ሁነው ቴዎዶሪጦስና ኢባን እንዲወጡላቸው «የንስጥሮስ መምህር ቴዎዶሪጦስ ይውጣ ቄርሎስ አውግዞታልና ቴዎዶሪጦስን ካስገባን ቄርሎስን እናስወጣ» እያሉ ተቃውሟቸውን ገለጡ ጥያቄያቸው መልስ ሳያገኝ ጉባኤው በጩኸት ስለቀለጠ የቤተ መንግሥቱ ጸጥታ አስከባሪ ጓድ ገብቶ ዝም አሰኛቸው::

ከዚህ በኋላ ልዮን በፊት ወደ ፍላብያኖስ የላከውና አሁን ወደዚህ ጉባኤ የላካቸው መልእክቶች ተነበቡ:: (ወደ ፍላብያኖስ የላከውን በመጀመሪያ አይተነዋል) አሁን እዚህ ላይ ደግሞ ወደ ጉባኤው በላከው ጦማር ውስጥ ልናውቀው የሚያስፈልገንን እናቀርባለን::

በጉባኤ ኬልቄዶን በተነበበው የልዮን ጦማር ውስጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ይገኙበታል::

1. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ ኋላም ሰው ሁኖ ተወለደ::
2. መለኮትና ሰብእና ብሉ ውስጥ ተገናኙ ባንድ አካል ውስጥ ያለመቀላቀል አብረው ይኖራሉ::
3. እያንዳንዱ ባሕርይ የግብር ክልሉን ጠብቆ ይኖራል ማለት መለኮት የመለኮትን ትስብእትም የትስብእትን ሥራ ይሠራል::
4. የሁለቱም ባሕርያት ሀብት ላንዱ አካል በእኩልነት ይገኛል::
5. ከመዋሐድ በፊት ሁለት ነበሩ፤ ከተዋሐዱ በኋላ ግን አንድ ባሕርይ ነው ማለት ሞኝነት ነው፤ የሚሉ ነጥቦች ይገኙበታል::

በዚህ ጦማር ውስጥ ከአንድ እስከ አምስት ተራ ቍጥር በዘረዘርናቸው ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ከመጀመሪያው በቀር አራቱ የሁለት ባሕርይን ትምህርት በይፋ የሚደግፉ ናቸው:: ይህንንም እንደሚከተለው እንገልጣለን::

በሁለተኛው ተራ ቍጥር ያየነው «ተገናኙ» «ተራከቡ» «አብረው ይኖራሉ» የሚለው ቃል ተዋሐደ በሚለው ግሥ የተለወጡ የንስጥሮስ ግሶች ናቸው:: እነዚህ ግሶች የሚያሳዩት የአምላክን ሰው መሆን የሰውን አምላክ መኾን አይደለም:: ጽምረት ነው እንጂ፤ እንደ ጎዳሪና ማኅደርና እንደ ባልና ሚስት «ተዋሕዶ» ግን እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ ነው:: በሦስተኛው ተራ ቍጥር እያንዳንዱ ባሕርይ የግብር ክልሉን ጠብቆ ይኖራል ያለው በተዋሕዶ የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል መሆኑንና መገናዘቡን፤ መወራረሱን ሲገልጥ ቅዱስ ቄርሎስ «እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል» ያለውን ለማስተባበል ነው:: ይህን የቅዱስ ቄርሎስን ትምህርት መለወጥ የሥጋዌን ምሥጢር ያፋልሳል፤ ግብር ይከፋፍላል:: በአራተኛው ተራ ቍጥር «የሁለቱም ባሕርያት ሀብታት ላንዱ አካል በእኩልነት ይገኛሉ» ማለት ደግሞ እንደ ሁለት እጅ እንደ ሚዛን ጆሮ ማለት ነው:: ይህንንም ልዮን በመደጋገም ክርስቶስ አንደ ጊዜ እንደ አምላክነቱ ሌላ ጊዜ እንደ ሰውነቱ ይሠራ ነበር እንጂ ባንድ ጊዜ የአምላክነትንም የሰውነትንም ሥራ አልሠራም ብሏል:: ይህም አስተሳሰብ በቃሉ አዞ በእጁ ይዞ የሠራውን የሥግው ቃል ተአምራት የሚያናውጠው ሁኖ ተገኝቷል::

ወደ ጉባኤው እንመለስና ይህ የልዮን ጦማር በተነበበ ጊዜ ከግሪኮች እንዳንዶቹ በችኮላ፤ ላቲኖችም «ይህች ሃይማኖት የአባቶቻችን ናት: ይህች ሃይማኖት የሐዋርያት ናት: ጴጥሮስ በልዮን አንደበት ትክክለኛይቱን ሃይማኖት መሰከረ እያሉ ጮሁ:: ነገር ግን ከላይ እንደገለጥነው ይህ ትምህርት የንስጥሮስና የልዮን ነው እንጂ የጴጥሮስ አልነበረም:: ጴጥሮስ አካል ከህልውና ተገልጦለት «አንተ ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው» የሕያው እግዚአብሔር ልጅ አንተ ነህ ብሎ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን በቂሳርያው ጉባኤ መስክሮ ፈተናውን ያለፈ አርበኛ ነው:: እንደ ልዮን የመለኮትህ ባሕርይ የእግዚአብሔር ልጅ ነው አላለም::

ዳግመኛም ቅዱስ ቄርሎስ «ቃል በሥጋ ሞተ» ብሎ ያስተማረው ከቅዱስ ጴጥሮስ ያገኘውን ትምህርት ነው:: «ሞተ በሥጋ ወሐይወ በመንፈስ» ብሎ ያስተማረ ቅዱስ ጴጥሮስ ነው «የሞትም የሐይወም ባለቤት ራሱ ሥግው ቃል ነውና ማለት ሞትም ትንሣኤም የሥግው ቃል ነው:: የልዮን ጦማር ግን የሚለው «ሥጋ ሞተ በኀድረተ አምላክ ቃል» ነው:: ይህም ማለት «ሞተ» የሚለው አንቀጽ ሥጋን ለይቶ ይመለከታል ማለት ነው:: ታዲያ ይህ ትምህርት እንዴት የጴጥሮስ ነው፤ የሐዋርያት ነው፤ ይባላል?

ይህ ጦማር ሲነበብ ያጨበጨቡ ቢኖሩም ባንጻሩ ከግብጽ ከሶርያና ከአርመን የመጡት ደግሞ በዚህ ንስጥሮሳዊ ትምህርት የማይስማሙ መሆናቸውን እየገለጡ ጉባኤውን አቋርጠው ወጥተው ሔዱ።

ግሪኮችና ላቲኖች ባንድ ወገን የቤተ መንግሥቱ ባለ ሥልጣኖች 'በሌላ ወገን እየሆኑ መስማት አለባችሁ እያሉ ቢያስፈራሯቸውም የልዮንን ጦማር የተቃወሙት ክፍሎች የሚመልሱት መልስ «ክርስቲያን ማንንም አይፈራም፤ ከእሳት ብትጥሉንም ስምደነዋል፤ ሰው ከተፈራ ሰማዕታት በቤተ ክርስቲያን ባልነበሩም ነበር።» የሚል ነው። ለነገሩማ እንዲያው ግሪኮችና ላቲኖች አፋቸውን በውሸት አበሳሹ እንጂ የልዮን ጦማር ንስጥሮሳዊ ለመሆኑ ምስክሩ ራሱ ንስጥሮስ ነው። ንስጥሮስ ከመሞቱ ቀደም አድርጎ ይህን የልዮን ጦማር አይቶ የሚከተለውን ተናግሮ ሙቷል። «ይህችን ጦማር አግኝቼ ባነበብሁ ጊዜ ደስ አለኝ እግዚአብሔርንም አመሰገንሁት የሮም ቤተ ክርስቲያን ንቀሩ የሌለበትን ትክክለኛ ሃይማኖት ተቀብላለችና» ብሏል። ያው የራሱን እምነት ልዮን ገልብጦ ስላጸደቀለት ነው፤ ነቀፋ የሌለበት ትክክለኛ ሃይማኖት ያለው። ነገር ግን ሞት ቀድሞት የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ አልሰማም ቢሰማ ኑሮ በጣም በተደበቀ ነበር።

አሁን በኋላ የተነሡ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አባቶቻቸው በኬልቄዶን ጉባኤ ያሳዩት ቅሌት እያሳፈራቸው የልዮንን ጦማር የተቀበልነው አርመን ነው ይላሉ። ነገር ግን ታሪክ የመዘገበው አጨብጭበው መቀበላቸውን ነው። (በእርግጥ ከተሰሎንቄና ከመቄዶንያ የመጡ ግሪኮች እንቀበልም ለማለት ሞክረው ነበር ይባላል) አርመነዋል የሚሉትም ውሸት ነው። ምክንያቱም ግሪኮች ያን ጊዜ ጓጉተው የሚጠባበቁት በማንኛውም መንገድ ልዮንን አስደስተው የእስክንድርያን ሊቃነ ጳጳሳት ስም አጥፋፍተው አክፋፍተው የኛ ነው የሚሉትን በመንበር ተራ ቊጥር ያልነበረውን የቊስጥንጥንያ መንበር ከቊጥር ለማስገባት ስለነበር ነው። አንዳንድ የተከራከሩ ቢኖሩም የቊስጥንጥንያ ቤተ መንግሥትና የልዮንን ኃይል ስለ ፈሩ አልገፋበትም። ደፍረው በልዮን ጦማር አንስማማም ያሉትም የደረሰባቸውን መከራ ወደፊት የምናየው ነው።

በጉባኤው የመጀመሪያ ስብሰባ ዲዮስቆሮስ ተወገዘ። ስለ ተወገዘበትም ምክንያት በተሰጠው መግለጫ «ዲዮስቆሮስ የተወገዘው በሃይማኖት ሳይሆን በሌሎች ሁለት ምክንያቶች መሆኑ ተገለጠ። እነዚህ አንደኛ ከሊቀ ጳጳሳት ጌታ ልዮን ጋር ባለ መስማማቱና ሁለተኛ ወደ ጉባኤው ሁለተኛ ተጠርቶ ባለ መምጣቱ እንደሆነ ተነግሯል። ከአውጋዦቹ አንዱ የቊስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ አናቶልዮም ይህንኑ ገልጧል።

ሲያያዝ በመጣው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አንድ የቤተ ክርስቲያን መምህር አባት፤ ከቤተ ክርስቲያን ተወግዞ የሚለየው ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመለሰው የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተፈጸሙ በኋላ ነው። ጉባኤ ይሰበሰባል ባለ ጉዳይ ይቀርባል፤ የባለ ጉዳይን አሳብ ሰምቶ ጉባኤው ይነጋገርበታል፤ ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ይሰጣል፤ ውግዘቱ ወይም ይቅርታው ከዚያ በኋላ ነው። በኬልቄዶን ጉባኤ ግን ይህ ሁሉ አልነበረም። ዲዮስቆሮስ ተከሳሽ መሆኑን አላወቀም፤ ሃይማኖቱንም አልተጠየቀም፤ ወደ ጉባኤው መጣ ጉባኤው ሥራ ከመጀመሩ በፊት እንዲወጣ ታዘዘ፤ ሃይማኖቱን መስክሮ ወጥቶ ሔደ፤ ከዚህ በኋላ በሌለበት ተወገዘ የተወገዘውም በሃይማኖት ሳይሆን ከልዮን ባለ መስማማቱና ወደ ጉባኤው ሲጠሩት አሻፈረኝ በማለቱ ነው የሚል መግለጫ ወጣ።

እዚህ ላይ ጉባኤ ኬልቄዶን በቤተ ክርስቲያን ያልተለመደና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የሚያፈርስ ወንጀል ፈጽሟል ለማለት ይቻላል። ይኸውም:-

አንደኛ፤ ከጉባኤ ማባረር ቤተ ክርስቲያን መናፍቃንን እንኳ መከራ አባብላ እምቢ ሲሏት እንጂ እንዲያው በማን አለብኝ እንዳትጠቀም ወንጌላዊ መመሪያ ያላት ናት። ዲዮስቆሮስ ግን ሐሳቡን የመስጠት መብት እንኳ ተነፍጎት ከጉባኤው ተባሯል። «ዲዮስቆሮስ ካለበት እኛ እንወጣለን» ብለዋልና።

ሁለተኛ፤ ውግዘት በሌለበት መፈጸም በዚህ ሁሉ ምክንያት ማለት ሲጠሩህ አልመጣህም፤ ከልዮን አልተስማማህም ብሎ ከማውገዝ ምክንያቱን መጠየቅ ይቀድም ነበር። ጥያቄን ካስቀደመ በኋላ በውነትም ከልዮን ጋር አለመስማማቱን ሰሞት የሚያበቃ ኃጢአት ሁኖ ካገኘው የመሰለውን ርምጃ ቢወስድ ጉባኤው እንዲህ አይዋረድም ነበር። በእርግጥ ዲዮስቆሮስ ሁለተኛ ሲጠሩት አልመጣም፤ መምጣትም አልነበረበትም አንድ የቤተ ክርስቲያን አባት ይልቁንም የታላቁ የመንበረ ማርቆስ ሊቀ ጳጳስ ዲዮስቆሮስ እንደ ሕፃን ሒድ ሲሉት የሚሔድ፤ ና ሲሉት የሚመጣ አይደለምና። የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ለሚያጠና ሁሉ እውነቱን ለመግለጥ የኬልቄዶን ጉባኤ በኢየሩሳሌም በ50 ዓ.ም እንደ ተደረገው ሐዋርያት ጉባኤ፤ እንደ ኒቅያ፤ እንደ ቊስጥንጥንያና እንደ ኤፌሶን ጉባኤ የሚነጋገርበት ራሱን የቻለ ርዕስ አልነበረውም። የንስጥሮስን የፍልስፍና ስም ለማደስና የእስክንድርያን መንበር ለማዋረድ የተደረገ የሥልጣንም ጉዳይ ያለበት ነው። ይኸውም እስከዛሬ የቤተ ክርስቲያ በሽታ ሁኗል።

ዲዮስቆሮስ ከተወገዘ በኋላ ንግሥት ብርክልያ በግል አስጠርታ ሐሳቡን እንዲለወጥ በልዮን ጦማር እንዲስማማ መከረችው። ዲዮስቆሮስ ግን የሚያምነውን የሚያውቅ መንፈሰ ብርቱ ነበርና እሺ አላላትም። በዚህ ጊዜ ጽሕሙ እስኪነጫጭና ጥርሶቹ እስኪወልቁ አስደበደበችው። እሱም መደብደቡን በአኰቴት ተቀብሎ የተነጨውን ጽሕሙንና የወለቁት ጥርሶቹን ባንድ ላይ ቋጥሮ «ዝንቱ ውእቱ ፍሬ ሃይማኖት» ይህ የሃይማኖት ፍሬ ነው» ብሎ በግብጽ ለሚኖሩ ምእመናን ልኮላቸዋል። ይህም ለእስክንድርያና ከዲዮስቆሮስ ጋር ሁነው በልዮን ጦማር ሳልተስማሙ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ለዓለማዊ የታሪክና የሰማዕትነት ቅርስ ሁኖ ይኖራል። ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ዐቢይ ዓምደ ሃይማኖት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት አርበኛ (አትሌትስ) የሚል ቅጽል ተሰጥቶታል። ከዚህ ሁሉ በኋላ ማለት ስድቡም መወገዙም መደብደቡም ካበቃ በኋላ በደሴተ ጋግራ እንዲታሰር ከንጉሡ ከመርቅያም ትእዛዝ ወጣ። በደስታ የስደቱንም ጉዞ ተጋተረው። በስደቱ ጊዜ ጴጥሮስና ቴዎፒስቶስ የሚባሉ ሁለት መነኮሳት ዲቆናት ብቻ ተከትለዉት ነበር። በስደትም እንዳለ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ሥራ አልፈታም ትምህርት አዘል መልእክቶችን እየጻፈ በመላክ የእስክንድርን ቤተ ክርስቲያን ሲያጽናናት ቆይታል። ምእመናንና መነኮሳትም በመምህራቸው ላይ የደረሰውን ግፍ እያስታወሱ በተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ጸኑ።

ዲዮቆሮስን ያወገዘውና እንዲሰደድም የተስማሙ ይህ ጉባኤ በልዮን ጦማር ላይ ብቻ ተፈራርሞ ስመበታተን አስቦ ነበር:: ነገር ግን ንጉሡ መርቅያን የለም፤ ከተሰበሰባችሁ በኋላ የራሳችሁንም የጋራ መግለጫ ሳታስሙ ልትሔዱ አትችሉም ስላላቸው ደንግጠው የጉባኤው ውሳኔ ነው በሚል ስያሜ አንድ አርቃቂ ቡድን ተቋቋመ:: ይህ የመጀመሪያው አርቃቂ ቡድን የተስማማበት «ክርስቶስ ከሁለት ባህርያት የተገኘ ነው» የሚል ሐረግ ነበረበት:: ነገር ግን ይህ ሐረግ ቄርሎስና ዲዮስቆሮስ የሚሉት ስለሆነ መኳንንቱ ተቃወሙ:: በዚህ ጊዜ ረቂቁ እንደገና ወደ ንጉሡ ቀረበ:: ንጉሡም ባስቸኳይ ይህ ተሠርዞ ሌላ ረቂቅ እንዲወጣ አዘዘ በመጨረሻም ከዚህ በሚከተለው ረቂቅ ተስማሙ::

1. አምላክ ፍጹም ወሰብእ ፍጹም፤ ኅቡር ህላዌ አብ በመለኮቱ፤ ኅቡረ ህላዌ ምስሌነ በትስብእቱ፣
2. እሙሩ በክልኤቱ ህላዌያት (ባሕርያት) ዘእንበለ ፍልጠት ውላዌ ወቱስሕት
3. በተዋሕዶ ኢያእተተ ፍልጠተ ማእከለ ክልኤቱ ህላዌያት (ባሕርያት)
4. ወሀብታተ ክልኤቱ ሕላዌያት ይትዐቀቡ በበህላዌሆሙ፤ ወእምክልኤሆሙ ይትረከብ አሐዱ አካል::

1. ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ፤ በአምላክነቱ ከአብ ጋር አንድ ነው በሰውነቱ ከኛ ጋር አንድ ነው::
2. በሁለት ባሕርያት የሚታወቅ፤ ያለመለየት፤ ያለ መለወጥ ያለ መቀላቀል
3. ተዋሕዶው በባሕርያት መካከል ያለውን ልዩነት አላጠፋውም
4. የሁለቱ ባሕርያት ገንዘቦች (ሀብቶች) በየባሕርያቸው ተጠብቀው ሁለቱም አንድ አካልን ያስገኛሉ::

ከዚህ በላይ ከአንድ እስከ አራት ተራ ቊጥር የተመለከቱት ነጥቦች ያሉበት አንድ ረቂቅ አውጥተው ተፈራርመው ለንጉሡ አቅርበዋል:: ይህ የሃይማኖት ረቂቅ ንባቡም ምሥጢሩም በዚህ ጉባኤ የተሰበሰቡት ሰዎች አይደለም፤ ንስጥሮስ ግልጥ አድርጎ «ሁለት አካል፤ ሁለት ባሕርይ፤ ሁለት ግብር አምላክ በማርያም ልጅ አደረ:: በተራክቦተ መለኮት፤ ወልደ ማርያም ወልደ አብ የመባልን ትርሲት አገኘ፤» ያለውን ልዮን ለማደራገር አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ሁለት ግብር ብሎ ምርቅና ፍትፍት አድርጎ ያቀረበላቸውን እነሱም በባለ ሥልጣኖች ተጎትጉተው ግማሹን ከቄርሎስ ግማሹን ከልዮንና ከንስጥሮስ ወስደው እንደ ሞዛይክ ደንጊያ ወይም እንደ ልመና ጥሬ ውጥንቅጥ፤ ላንባቢ ለተርጓሚ አሻሚ አደናጋሪ፤ ገበሬ አስደንግጥ አድርገው አቅርበውታል:: ይህንንም በየተራ ባጭር ባጭሩ እንመለከተዋለን::

በተራ ቊጥር አንድ ያለው ንባብ ከቄርሎስ የተወሰደ ነው:: እነሱ ግን «አምላክ ወሰብእ» የሚለውን ንባብ ለሁለት ባሕርይ ምስክር አድርገው ወስደውታል:: ዘይቤውን ከነምሥጢሩ ከነምስክሩ ለሚያውቅ ግን «አምላክ ወሰብእ» የሚለውን ንባብ ሁለት ባሕርይ አይነካካውም «ወ» እዚህ ላይ አጫፋሪ አይደለም:: «ሰማይ ወምድር» ሰማይና ምድር፤ «መላእክት ወሰብእ» ሰውና መላእክት፤ እንዳለው «አምላክ ወሰብእ« የሚለውም ንባብ» አምላክና ሰው» ተብሎ በምሥጢረ ሥጋዌ አይፈታም «ወ» እዚህ ላይ «ዋዌ» ነው:: «ድንግል ወእም» እንዳለው፤ ፍችው እናትም ድንግልም ማለት ነው፤ እናትና ድንግል አይባልም:: «አምላክ ወሰብእ» ማለትም በምሥጢረ ሥጋዌ «አምላክም ሰውም» ተብሎ ይፈታል እንጂ «አምላክና ሰው» ተብሎ አይፈታም:: ጽርዓውያን ግን አገባባቸው ሰፊ ስለሆነ በዋዌው ፈንታ ከሁለቱ ስሞች አንዱን ጎርደው «ቴዎስ (አምላክ) አንትሮፖስ (ሰው) «ያለውን ቴአንትሮ ፖስብለው ያናብቡና በቅጽልም በዋዌወም ይፈቱታል:: በዋዌ ሲፈታ እንደ ግእዙ ነው:: በጥቅልነት ሲፈታ ግን ሰው የሆነ አምላክ ማለት ነው:: ይህን የመሰለ ብዙ ንባብ አላቸው ክርስቶስ፤ ሰው የኾነ አምላክ እንጂ አምላክ የሆነ ሰው አይባልም:: ይህ ከሆነ ጳውሉስ ሳምሳጢና ንስጥሮስ እንዳሉት በገድል በትሩፋት የከበረ ዕሩቅ ብእሲ ነው ያሰኛልና::

በሁለተኛው ተራ ቊጥር «በሁለት ባሕርያት የታወቀ የሚለው በግልጥ መልኩን ሳይለውጥ የገባ የንስጥሮስ ንባብ ነው:: ያለ መለየት ያለመለወጥ፤ ያለ መቀላቀል የሚለው ምንታዌን ለመሸፈን የገባ ነው::

በሦስተኛው ተራ ቊጥር ያለው ንባብ «ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ» «በተዋሕዶ ሁለትነት ጠፋ» የሚለውን ትምህርት የሚያፋልስ ነው:: የመጨረሻውና አራተኛው ደግሞ ባለፈው በልዮን ጦማር ያየነው ነው፤ ያንኑ መመልከት ይበቃል::

በጉባኤው መጨረሻ ላይ ንጉሡ መርቅያንና ንግሥቲቱ ብርክልያ ወደ ጉባኤው አዳራሽ ገቡ:: በዚህ ጊዜ የተሰበሰቡት ሁሉ በደስታና በዕልልታ ተቀበሏቸው:: ንጉሡ ከዚህ አያይዞ የሚከተለው ተናገረ:: «በነገሥታቱ ሲደረግ እንደ ነበረው ሁሉ እኔም የንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን ከያዝሁ ጀምሬ የሃይማኖት ጉባኤ እንዲደረግ ምኞቴ ነበር» ሲል ለጉባኤው አሰማ:: ጉባኤውም ለንጉሡና ለንግሥቲቱ ውሳኔው ካስረዳ በኋላ ንጉሡን የሃይማኖት የበላይ ጠባቂ አድርገው ዳግማዊ ቆስጠንጢኖስ ብለው ሰይመውታል::

ይህ ጉባኤ በምሥራቃውያን ዘንድ ጉባኤ አብዳን ጉባኤ ከለባት ይባላል:: ውሳኔውን የተቀበሉ አብያተ ክርስቲያናትም መለካውያን ይባላሉ፤ ንጉሣውያን፤ ፈጻምያነ ፈቃደ ንጉሥ፤ ንጉሥ ያሉት ትክክል ነው ባዮች የቤተ መንግሥት ራት አግባዎች ማለት ነው:: አብዳን ከለባት መባላቸውም በፊት ሐዋርያት ኋላም ሊቃውንት እነ አትናቴዎስ፣ እነ ዮሐንስ አፈወርቅ እነ ቄርሎስ ጠብቀው ያቆዩትን የቤተ ክርስቲያን መብት በቊስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት አስረክበዋልና እነዚህ መለካውያን 30 አንቀጾች ያለው ቀኖናም ሠርተዋል፤ በዚህ ቀኖና በ28ኛው አንቀጽ «የቊስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ለሮሙ ሁለተኛ እንዲሆን ተፈቅዶለታል:: ቊስጥንጥንያ አዲስ ሮም ስለሆነች» ይላል:: በዚህ ንባብ ግሪኮች የተመኙነውን አገኘን ብለው ደስ ሲላቸው ልዮን ግን ይህንን ቀኖና አልተቀበለውም::

ወደ እስክንድርያ እንመለስና ዲዮስቆሮስ በደሴተ ጋግራ በእሥር እንዳለ የቊስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት ከሮማው ፓፓ ጋር በመነጋገር ፕሮቴሪዮስ የሚባለውን መለካዊ መነኲሴ የእስክንድርያ ፓትርያርክ እንዲሆን ሹሞ ላከው:: ነገር ግን ዲዮስቆሮስ ቢታሰርም ምእመናኑና ካህናቱ አባታችን ነው ብለው የሚያምኑት ዲዮስቆሮስን ስለሆነ አዲሱን ፓትርያርክ አንቀበልም አሉ:: በዚህ ምክንያት መርቅያን ተናዶ እሱ የሾመውን ያለ ምክንያት በግድ እንዲቀበሉ ለማድረግ 2ሺህ ጦር ወደ ግብጽ ላከ:: ነገር ግን የሕዝብን ተቃውሞ የጦር ኃይል ስለማይመልሰው የምእመናኑ ኃይል እየበረታ ሔደ:: ብጥብጡም ውስጥ ፕሮቴሪዮስ ተገደለ:: በመካከሉ በ454 ዓ.ም

የተዋሕዶ አርበኛው ዲዮስቆሮስ በእስር እንዳለ ዐረፈ:: እሱ ካረፈ በኋላ ሦስት ዓመት ቆይተው የግብጽ ምእመናን ራሳቸው መርጠው ጢሞቴዎስ የተባለውን አባት ፓትርያርክነት ሾሙት:: እሱም ለተዋሕዶ እምነት ተቆርቋሪ፤ የቄርሎስ የዲዮስቆሮስ ተከታይ ስለ ነበር በዲዮስቆሮስ መታሰር ታውካና ተበጥብጣ የነበረችው እስክንድርያ በእርሱ መሾም ተጽናናች፤ ተረጋጋች::

<u>ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ</u>

ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ለሚቀጥሉት 150 ዓመታት ያህል የነገሡ የቍስጥንጥንያ ነገሥታት ቤተ ክርስቲያንን ለማዋሐድ ብዙ ጥረት አድርገዋል:: ለምሳሌ ከ474 - 491 ዓ.ም የነገሠው ዘይኑን (ዚኖን) ከ491 - 518 ዓ.ም የነገሠው አንስታስዮስ በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ የሚለውን የተዋሕዶ እምነት ተቀብለው ቤተ ክርስቲያን በሰላም የምትመራበትን መንገድ ለመፈለግ ተነሳስተው ነበር:: ለዚህም በጎ ፈቃድ መሰናክሉ የኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔና የልዮን ጦማር መኾኑን በመገንዘብ የቍስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ አባ አጋግዮስ (አካኪያስ) እና ንጉሡ ዘይኑን ተስማምተው ይህን ለመሠረዝና ቤተ ክርስቲያንንም ወደ ጥንታዊ የተዋሕዶ እምነቷ ለመመለስ ከአንጾኪያውና ከእስክንድርያው ፓትርያርኮች ጋር ውይይት ጀመሩ::

በዚህ የአጋግዮስ የዕርቅ ድርድር የእስክንድርያውም የአንጾኪያውም ፓትርያርኮች ተስማምተው ፈርመዋል:: በዚህ ጊዜ የሮማው ፓፓ እኔ ሳልጠየቅ ይህ እንዴት ይሆናል? በማለት ተቆጥቶ ሊቀ ጳጳሱን አጋግዮስንና ንጉሡን ዘይኑን አወገዛቸው 488 ዓ.ም በዚህ ምክንያት የሮምና የቍስጥንጥንያ አብያተ ክርስቲያናት ለ30 ዓ.ም ያህል ተኳርፈው ኑረዋል በነዚህ 30 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በሶርያና በአንጾኪያ የቄርሎስን ትምህርት የሚደግፉ በሙያ የበሰሉ ለተዋሕዶ ሃይማኖት ተቆርቋሪዎች እነ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያና እንፍልክስዩስ (ፊሎክሴኖስ) ዘሶርያ ለተዋሕዶ እምነት ለመመስከር በቆራጥነት ተነሡ::

ሳዊሮስ ከ465 - 538 የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ ኾኖ የመለካውያንን ብዛትና ዛቻ ሳይፈራ ሳያፍር ምሥጢረ ተዋሕዶን ያስተምር የነበረው ነው::

ፊልክስዩስ (ፊሎክሴኖስ) ደግሞ 512 - 518 በማቡግ ሶርያ ኤጲስቆጶስ ሁኖ መለካውያን ከተዋሕዶዎች ጋር አፍላ ጦርነት ባደረጉበት ጊዜ በትምህርት ተዋግቶ በከፊልም ቢኾን መለካውያን የማረኳቸውን ምእመና መልሷል::

በ491 ዓ.ም በቫግሃፓት የተደረገው ጉባኤ የተዋሕዶ እምነት የአርማንያ ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን የተወሰነው እነዚህን በመሳሰሉ የሃይማኖት አርበኞች ትግል ነው::

የተዋሕዶ ሃይማኖት በነዚህ ጊዜያት አልፎ አልፎ ድል ቢያጋጥመውም፤ አንዳንድ መሰናክልም ኣላጣውም፤ የቤተ ክርስቲያንን አንድ መሆን የማይደግፉ መለካውያን ከላይ የሮማውን ፓፓ ትራስ አድርገው በቤተ ክርስቲያን የውስጥ ብጥብጥ ከመፍጠር አልተቆጠቡም: በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ማለት ከኬልቄዶን ጉባኤ በፊት በማንኛውም የጸሎት ጊዜ» ቅዱስ እግዚአብሔር፤ ቅዱስ ኃይል፤ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ከተባለ በኋላ በየእርከኑ ዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሠሃለነ እግዚኦ:: ዘተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ፤ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት፤ ይኮንን ሕያዋነ ወሙታነ ተሠሃለነ እግዚኦ» እየተባለ ምሥጢረ ሥጋዌን ከልደት እስከ ዳግም ምጽአት የተደረገውን ሁሉ ያነሣል:: ቅዱስ እግዚአብሔር ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት የሚለው ቃል በቤተ ክርስቲያናችን አባቶች እንደሚተረከው ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታን በሚገንዙበት ጊዜ ሲጸልዩት የነበረ ነው:: ሌላው መርገፉ የኒቅያ አንቀጸ ሃይማኖት ነው:: መለካውያን ግን ቆነጻጽለው ጥሰው ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃይል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ካሉ በኋላ ተሠሃለነ እግዚኦ ይላሉ:: ቅዱስ እግዚአብሔር ተወለደ፤ ተጠመቀ፤ ተሰቀለ፤ ሞተ ማለት ወደ ቄርሎስ ትምህርት እንዳይወስዳቸው ነው:: በ512 ዓ.ም በአናስታሲዮ ዘመነ መንግሥት የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ ሳዊሮስ እንዳጋጣሚ በቍስጥንጥንያ ተገኝቶ በቤተ ክርስቲያን እንደ ጥንቱ ትውፊት ሲጸልይ መለካውያን ካህናትና ኤጲስ ቆጶሳት ባንድ ላይ ሁነው ጮሁበት:: ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ይህ ጸሎት በመለካውያንና በተዋሕዶዎች መካከል በመለያ መልእክት ሆነ::

የነዚህ የሁለቱ ነገሥታት ዘመን በተከታታይ ሲያልፍ ማለት የዘይኑንና የአናስታሲዮስ ዘመን ሲያልፍ ከ518 - 527 ዓ.ም የነገሠው የጁስቲንና ከ527 - 565 የነገሠው የወንድሙ ልጅ የጁስቲኒያን ዘመን መንግሥት ተተካ:: ጁስቲን የግሪኮች ንጉሥ ይሁን እንጂ ላቲን ከሚናገሩ ሮማውያን የተወለደ በሮማዊነቱ የሚያምን ስለነበረ ለ30 ዓመታት ያህል ተኳርፈው የነበሩትን የግሪክንና የሮማን አብያተ ክርስቲያናት አስማማ:: ከሱ በፊት የነበረውን የእርቅ መሠረት ሁሉ ደምስሶ የቄርሎስን ትምህርት የተቀበሉት ሁሉ የልዮንን ጦማር እንዲቀበሉ በተቻለው ሁሉ ጥረት ጀመረ:: ጁስቲን ጥረቱ ሳይሳካ ሞተ፤ የተዋሕዶ እምነት ግን አልሞተችም አሁንም አለች::

ጁስቲን ከሞተ በኋላ ወራሾቹ እነ ጁስቲኒያን እንደ ገና የተቻላቸውን ሁሉ አደረጉ፤ አሁንም አልሆነላቸውም:: እንዲያውም «ጀግና የሚወለደው በጦር ሜዳ ነው» እንደሚባለው በጁስቲኒያን ዘመን ነው በምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያጥቢያ ኮከብ የሆነው ያዕቆብ ዘአልበረዲ የተነሣው:: ያዕቆብ ዘአልበረዲ ሶርያዊ መነኩሴ ነው:: የተወለደውም በዚሁ በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው:: የተወለደባት ልዩ መንደር ቴላ ትባላለች የሶርያ ዕጻ ናት:: ከዚያ ለትምህርት ወደ ቍስጥንጥንያ ሔዶ ሲማር ከቆየ በኋላ በዚችው በቍስጥንጥንያ መነኮሰ «አልበረዲ» የቅጽል ስሙ ነው:: በርዱና ማለት በዐረብኛ በቅሎ ማለት ነው:: እንደ አጋሰስ መደላድል የሚሻክር ልብስ ለብሶ ያስተምር ነበርና:: አንድም እንደ በቅሎ የሚሰግር ፈጣን ማለት ነው:: ሰረገላ ሰጋሪ ሰጋር እንደ ማለት:: መለካውያን ያስድዱት የነበረውን የተዋሕዶ እምነት ደጋፊ ስለነበር በዘመኑ ከነበሩት የፓለቲካና የሁለት ባሕርይ መለካውያን መሪዎች እየተደበቀ ድሪቶ ለበሶ አልባሌ መስሎ የአባቶቹን የእነ አትናቴዎስን የቄርሎስንና የዲዮቆሮስን እምነት ያስተምር ነበር:: (የኛ አባቶች ግን የሴት ቀሚስ ሳይቀር ለብሶ ያስተምር ነበር ይላሉ) ያዕቆብ እየተደበቀ ያስተምር በነበረበት ጊዜ እንዳጋጣሚ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቴዎዶስዮስ በንጉሡ በጁስቲኒያን ትእዛዝ ወደ ቍስጥንጥንያ ተይዞ እንዲመጣ ተደረገ በቍስጥንጥንያ በቁም እሥር ላይ ይገኝ ነበር በ538 ዓ.ም::

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ያዕቆብ ዘእልበረዲና ፓትርያርክ ቴዎዶስዮስ ከዚች ከተማ ተገናኙ:: ያዕቆብ ለተዋሕዶ እምነት የሚያደርገውን ተጋድሎ በመገንዘብ ፓትርያርኩ በቁም እሥር ላይ እንዳለ እሱንና አባ ቴዎድሮስ የተባለ ጓደኛውን በሶርያ ለሚገኙ ሁለት ሀገረ ስብከቶች ኤጲስ ቆጶሳት አድርጎ ሾማቸው በ443:: ያዕቆብ ወዲያው እንደ ተሾመ ከጓደኛው ጋር ሁኖ ምድረ ሶርያን እየዞረ የተዋሕዶን እምነት ማስተማር ጀመረ:: ከትምህርቱና ከምሳሌነቱም የተነሣ ተዳክሞ የነበረው የተዋሕዶ ሃይማኖት እንደገና አንሰራራ፤ በዚህ አኳኋን ሶርያንና ግብጽን ለአርባ ዓመታት ያህል እየተዘዋወረ አስተምሯል:: በጉዞውም አብረዉት የሚዞሩና የሚረዱት ኮኖብና ኤብጊኒዮስ የሚባሉ ሁለት መነኮሳት ነበሩ:: ምእመናን እየበዙ ትምህርቱም እየተስፋፋ በመሔዱ ካህናትና ኤጲስ ቆጶሳት በብዛት ስለ አስፈለጉት ለእነዚህ ሁለት መነኮሳት የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ እንዲሰጥለት በግዞት ላይ ወደሚገኘው ወደ ፓትርያሪክ ቴዎዶስዮስ ላካቸው:: እነሱ ኤጲስ ቆጶሳት ሁነው ከመጡለት በኋላ ከነሱ ጋር ሁኖ 27 ጳጳሳትና ከአንድ ሺህ በላይ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሹመዋል::

ያዕቆብ ዘእልበረዲ አባትነቱ ለተዋሕዶ ልጆች ሁሉ መሆኑ ቢታወቅም ብዙ የተጋደለው በመለካውያን ጨርሳ ተደምስሳ በነበረችው በሶርያ ነው:: ይህ ሁሉ ሲሆን ያዕቆብ የሶርያን መንበረ ፓትርያርክ ለያዝ አላለም:: ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ በመለካውያን ተንከል ተሰዶ በግብጽ ሲሞት ያዕቆብ ከሌሎች ጳጳሳት ጋር ሁኖ ሰርግዮስ ሦስት ዓመት ቆይቶ ሲሞት በተባሕትዎውና በትሩፋቱ የታወቀውን አባ ጳውሊ የተባለውን ሾመው:: ያዕቆብ ዘእልበረዲ ሐዋርያዊ መልእክቱን ባለ መሰልቸት እየተጋደለ ከፈጸመ በኋላ በ578 ዓ.ም ዐረፈ::

ይህ አባት የምሥራቅ ቤተ ክርስቲን አክሊል ነው:: ለተዋሕዶ እምነት የሠራቸው ሥራዎች ለተዋሕዶ ሃይማኖት ልጆች ሁሉ መንፈሣዊ ወኔን ይቀሰቅሳሉ:: በተለይ በሶርያ ያሉ ምእመናን ሃይማኖታቸው ሊጠፋ ከቀረበ በኋላ ተነሥቶ ስላስደሰታቸው ለመታሰቢያው ይሆን ዘንድ የሶርያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያዕቆባዊት ትባላለች ምእመናኑም ያዕቃባውያን ይባላሉ:: ከዚያ በኋላ የተዋሕዶ እምነት በመጥፋት ፈንታ እየተስፋፋች ከታናሽ እስያ ጀምሮ ማለት ከጥቁር ባሕር ጀምሮ እስከ ዓባይ ወንዝ ድረስ ብዙ ተከታዮችን አፈራች:: በኢትዮጵያም የተዋሕዶ ሃይማኖት ብሔራዊት ሁና እስካሁን ቆይታለች::

መለካውያን ከኬልቄዶን ውሳኔ በኋላ የርስ በርስ ትርምስና አለመግባባት አጋጥሟቸዋል:: በተለይም በኬልቄዶን ውሳኔ ቀኖና 28 ላይ የሠፈረውን:: ልዮን አላጸድቅላቸውም በማለቱ ግሪኮች የልዮንን ጦማር በመደገፋቸው ብዙ ጸጸት አጋጥሟቸዋል:: ይሁን እንጂ ከላይ እንዳየነው የዘርና የፖለቲካም ጉዳይ ስላለበት ጠቡ አልተፋፋመም ከኬልቄዶን በኋላ ሁሉም ባንድ ላይ ሦስት ጊዜ ጉባኤ አድርገዋል:: እነዚህም ሦስት ጉባኤያት አንደኛ በ553 ዓ.ም የተደረገው ሁለተኛው የቊስጥንጥንያ ጉባኤ በመባል የታወቀው ነው:: ሁለተኛ ከ680 - 681 ዓ.ም በቊስጥንጥንያ የተደረገው ሦስተኛው የቊስጥንጥንያ ጉባኤ በመባል የታወቀው ነው:: ሦስተኛ በ787 ዓ.ም በኒቂያ የተደረገው ሁለተኛው የኒቅያ ጉባኤ በመባል የታወቀው ነው:: ባጠቃላይ መለካውያን ባንድነት የሚቀበሏቸው ሰባቱ ጉባኤያት እነዚህ ናቸው:: እኛ ግን ከኬልቄዶን ጉባኤ በፊት የተደረጉትን ሦስቱን ጉባኤት ብቻ እንቀበላለን እነሱም የኒቅያ የቊስጥንጥንያና የኤፌሶን ጉባኤያት ናቸው::

የሮም መንግሥት ምዕራቡና ምሥራቁ ባንድ ላይ ሁኖ በተዋሕዶዎቹ ላይ መከራ ሲያጸና የነበረውን ያህል ብድራትን የማያስቀር እግዚአብሔር በሱም ላይ እያከታተለ የሚያመጣበትን መከራ እንመለከታለን::

በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሮም ግዛት ምዕራቡ ክፍል እንደ ወደቀ ምሥራቁ ክፍል ደግሞ በሰባተኛው መቶ ዓመት መጀመሪያ ላይ በፋርስ ጦር ተወረረ:: (በ608 - 610) ይህ ሁሉ የመከራው ፊታውራሪ ነው:: በዚህ ጊዜ ውስጥ የግብጽና የሶርያ ቤተ ክርስቲያን በሳዊሮስ ዘአንጾኪያ ትምህርተ ሃይማኖት ተስማምተው በሐዋርያዊ ጉዞ ይገሥግሡ ነበር፤ (በ612 - 629) የሮም ግዛትና መንግሥት ግን አሁንም ንሥሐ አልገባም ላቲንና ግሪክ ያልሆኑት ወይም የሮም መንግሥት ባለ ሥልጣኖች የተቀበሉትን ዶግማ ሳይቀበሉ የተገኙ ሁሉ እየተያዙ በጭካኔ ይደበደቡ ነበር:: በተለይም በዚያ ዘመን የነበረው መለካዊ ንጉሥ ሕርቃል አገሩን ከወረሩት የፋርስ ወታደሮች ጋር ተዋግቶ ቢሸነፍ ተዋሕዶዎች የፋርስን ጦር ያስነሡበት ይመስል በግብጽ፣ በሶርያ፣ በፍልስጥኤምና እንዲሁም በቊስጥንጥንያ አንዳንድ ተዋሕዶዎች ቢኖሩ እነሱን እየለቃቀመ ይፈጃቸው ጀመር:: ግማሾቹም እየተመረሩ መለካውያን እንዲኾኑ ግብር ያጸናባቸው ነበር:: በተለይ የተዋሕዶዎች ኃይል በበረታበት በግብጽ እሱም ኃይሉን አበረታ ግብር መክፈል ያቃታቸው ንዋየ ቅድሳት እየሸጡ ይሰጡ ነበር:: ቢቸግራቸው ፓትርያርኩ አቡነ ቢንያም በዋሻ ተደብቀው አያሌ ዘመናት አሳልፈዋል::

ተዋሕዶዎች በዚህ ስቃይ እንዳሉ የፋርስ ጦር መጥቶ ግብጽን ወረራት (በ616) ኋላም በ639 ዓ.ም እስላም ዐረቦች መጡ:: በዚህ ጊዜ የሮም ነገሥታት ያገዛዝ ቀንበር ያሰቀቃቸው ተዋሕዶቾች በራቸውን ከፍተው ተቀበሏቸው:: አቡነ ብንያምም ከተደበቁበት ዋሻ የወጡት ለጊዜው እስላሞቹ ስለ ግብር ባደረጉት የምሕረት አዋጅ ነው:: ነገር ግን የግብጽን ምእመናን ስለ ተዋሕዶ እምነታቸው ከዚያ የባሰ እንጂ የቀለለ መከራ እሳካሁን አላጋጠማቸውም:: በገዛ አገራቸው እንደ ስደተኞች ኾነው የክርስቶስን መስቀል ተሸክመው ይኖራሉ::

ግሪኮችና ላቲኖች በሃይማኖት ስም የዘርና የሥልጣን ትግላቸውን ሲያካሒዱ ብዙ ጊዜ ቆይተዋል:: በ1ሺ14 ዓ.ም የሮማው ፓፓ ቤኔዲክቶስ ስምንተኛ በቀኖና ሃይማኖት (በጸሎተ ሃይማኖት) መንፈስ ቅዱስን ዘሠረጸ እም አብ ወእምወልድ «ከአብም ከወልድም የሠረጸ ነው» የሚለውን ሥርዋጽ አስገባ:: በዚህ ጊዜ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ተቃውሞ አላሰማችም:: ከአርባ ዓመት በኋላ 1054 ዓ.ም በዚሁና በሌሎችም ምክንያቶች የግሪክና የሮማ ቤተ ክርስቲያኖች በውግዘት ተለያዩ:: ከዚያም በኋላ ሮማም የራሷን ቤት ሰቦች ይዛ ለብቻዋ ግሪክም የራሷን ቤተሰቦች ይዛ ለብቻዋ ሆነች ሁለቱም አንዱ ሌላውን መናፍቅ በሚል ስም ይጠራሩ ጀመር::

የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ቢዛንታይን እየተባለ ከሚጠራው (ቢዛንታይን የሚባለው በቊስጥንጥንያ ያንድ መንደር ስም ነው:: ነገሥታት የሚወለዱበት መንደር ስለኾነ መላው የታናሽ እስያ መንግሥት ቢዛንታይን እየተባለ ይጠራ ነበር::) መንግሥቷ ጋር የቃል ኪዳን አባል ኾና ብዙ ሀገረ ስብከቶችን አስፋፋች:: ለምሳሌ «ሩሲያ፣ ዩጎዝላቪያ፣ ቡልጋርያ፣ ሩማንያና ሌሎችም የቦልካን አገሮች አብያተ ክርስቲያናት በግሪክ ቤተ ክርስቲያንና በቢዛንታይን መንግሥት የተመሠረቱ ናቸው:: ኋላ ግን የቢዛንታይን መንግሥት እየተዳከመ መጥቶ በ1453 ዓ.ም በቱርክ እስላም ኃይል ሲደመሰስ የቤተ ክርስቲያኒቱም ሀገረ ስብከቶች እየተጣበቡ ሔዱ::

በ1589 ዓ.ም የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ፓትርያርክ ሾመች:: የዩጎዝላቪያ (ሴርቢያ) ቤተ ክርስቲያን በ1920 ዓ.ም የሩማንያ ቤተ ክርስቲያን በ1925 ዓ.ም የየራሳቸውን መንበረ ፓትርያርክ አቋቋሙ:: በዚህ ሁኔታ የቊስጥንጥንያ መንበር ብቻውን ቀረ::

በምሥራቁ ያለው የመለካውያን ጉዞ ይኽ ሲሆን በምዕራቡ ክፍል ደግሞ እስላሞችን ከኢየሩሳሌም ለማስወጣት የሮማ ፓፓዎች የቫቲካን መሪዎች ነገሥታትንና መሳፍንትን እየቀሰቀሱ በተደጋጋሚ ከአሥራአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምረው ስድስት ጊዜ የመስቀል ጦርነት ማድረጋቸው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቧል:: በዚህ ጦርነት የምሥራቅ ክርስቲያኖች አልተባበሯቸውም እንዲያውም ጦሩ የሚመራው በካቶሊኮች ስለ ነበር ድል ያጋጠማቸው እንደሆነ እንደማይለቋቸው አውቀው ካቶሊኮችን በመጥላት እስላሞን ይደግፉ ነበር:: ካቶሊኮችም በመስቀል ጦርነታቸው ብዙ ድል አላጋጠማቸውም እስላሙንም ለማስወጣት አልቻሉም:: ነገር ግን የምሥራቃውያኑን ክርስቲያኖች ይዞታ እየነጠቁ በራሳቸው ስም አስመዝግበዋል:: በአሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (1439 - 1442) ፍሎርንዳ እስላም ቱርኮችን ለመከላከል የተደረገው የምሥራቃውያንና የምዕራባውያን ያንድነት ጉባኤ የፈረሰው በዘርና በሥልጣን በነበረው ልዩነት ምክንያት ነው::

የምዕራቡን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽታ የለወጠው የሉተር መነሣት ነው:: (1463 - 1546) ከሱም በኋላ ተከታዮቹ ብዙ የተለያዩ ለውጦችን በምዕራብ ቤተ ክርስቲያን አስገብተዋል::

የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት በመባል የታወቅነው፤ ወይም ክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው በማለት ከመለካውያን የተለየነው ክርስቲያኖች በ325 ዓ.ም በኒቅያ የተላለፈውን በ381 ዓ.ም በቊስጥንጥንያ የተላለፈውን ውሳኔ በ431 ዓ.ም በኤፌሶን የተላለፈውን ውሳኔ የምንቀበል መሆናችን ባለፈው ተገልጧል:: ከዚያ በኋላ ግን የግሪክ ቤተ ክርስቲያንና የሮማ ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ባንድ ላይ ኹነው የሚከተሉት ጉባኤዎች ይቀበላሉ::

ሀ/ በ451 የተላለፈውን የኬልቄዶን ውሳኔ፤
ለ/ በ553 በቊስጥንጥንያ የተላለፈውን ውሳኔ፤
ሐ/ በ681 በቊስጥንጥንያ የተላለፈውን ውሳኔ፤
መ/ በ786/7 የተላለፈውን የኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ፤ ይቀበላሉ:: ይህም ከፊተኛው ከሦስቱ ጋር ሲደመር 7 ጉባኤ ይሆናል:: እንግዲህ ካቶሊኮችና የምሥራቅ መለካውያን በነዚህ በሰባቱ ጉባኤያት አንድ ናቸው::

ከዚህ በኋላ ግን የሮማ ካቶሊክ ለብቻዋ ያደረገቻቸውን ጉባኤዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ መዝግባቸዋለች:: እነዚህ ጉባኤዎች አሥራ አምስት ናቸው::

በኬልቄዶን ጉባኤ ከተወሰነው ኢሕጋዊ ውሳኔ በኋላ የመለካውያንና የተዋሕዶዎች አቅዋም በዘመናት ሁሉ በጠላትነትና በመነቃቀፍ ነበር:: ከኬልቄዶን ውሳኔ በኋላ እኛም እነሱን ንስጥሮሳውያን መለካውያን ሁለት ባሕርይ ባዮች ይሉናል:: አንድ ባሕርይ ባዮች የሚሉንም ከሁለት መናፍቃን ጋር አጣምረው ነው:: አንደኛ «የእግዚአብሔር ቃል ሥጋን እንጂ ነፍስን አልተዋሐደም» ከሚል ከአቡሊናርዮስ (አፓሊናርዮስ) ጋር አዛምደው ነው:: በነሱ አባባል ክርስቶስን አንድ ባሕርይ የሚለው ትምህርት የአቢሊናርዮስ ነው፤ ቁርሎስም አንድ ባሕርይ ማለቱ በጥቅሱ ሳይጠነቀቅ ቀርቶ ነው ይላሉ::

ሁለተኛ ደግሞ ቃልና ሥጋ በተዋሐዱ ጊዜ ቃል ሥጋን መጦታል፤ ለውጦታል ከእሳት እንደ ገባ ቅቤ አቅልጦታል፤ ከሚለው ከአውጣኪ ጋር አጣምደው ነው:: ግሪኮች ዛሬም እኛን ባዩ ቊጥር አንድ ባሕርይ ባዮች ናችሁ ይሉናል:: ሌሎች ግን አምስቱንም እኅት አብያተ ክርስቲያናት በተንኮል ለመከፋፈልና ለመለያየት የእኛን ተማሪዎችና መነኮሳት ሲያገኙ ሌሎች ናቸው እንጂ እናንተ ሞኖፊሴት አይደላችሁም በማለት ያንዳንድ የዋሆችን ልቡና ከፋፍለውታል:: በተለይም እኛ ኢትዮጵያውያን ከራሳችን ሊቃውንት የተጻፉ መጻሕፍትን ሳንመለከት ወደ ውጭ ስለምንላክ እነሱ የሚሉት እውነት የሚመስለን ብዙዎች ነን::

በእርግጥ የኢትዮጵያ፣ የግብጽ፣ የሶርያ፣ የአርመንና የሕንድ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው በማለት ከኬልቄዶን ጉባኤ የተለዩ ናቸው:: ክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው የምንለውም እንደ አቡሊናርዮስ ከፍለን፤ ቀንሰን እንደ አውጣኪ አጣፍተን ሳይሆን እንደ ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ በባሕርይ ተዋሕዶ ነው:: በዚህም እንደ አትናቴዎስ፤ እንደ ቁርሎስ እንደ ዲዮስቆሮስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ባዮች ብንባል አንቆጣም:: በዲዮስቆሮስ አባትነት በአንድ አካል አንድ ባሕርይ እምነት አናፍርምና::

---

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

\- ተፈጸመ -